ከትናንት እንማር

/ግልፅ መልዕክት ለአንድነት አባላት/

ራሳቸው መሪ የሆኑበት ወይንም የሆኑበት ፖርቲ ህጋዊ ዕውቅና እንዳያገኝ እጥብቀው የታገሉ፣ ከዚህ አልፈውም ልንከሰስ ስለሆነ ቅንጅትን እንተወውና በየጎጆአችን ገብተን እንመሸግ ያሉ፣ ይህ ሃሳብና ፍላጎታቸው ተቀባይነት ቢያጣ ጥቂት ተከታዮቻቸውን አስከትለው ተግባራዊ ያደረጉና ይህንንም እንደ ጀብድ ያወሩት በጉባኤ «የተመረጡ»ነበሩ፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲ ለፍትህ በሚል ስያሜ ለመንቀሳቀስ የወሰኑት ወገኖች በቅርቡ ጠ/ጉባኤ እንደሚጠሩ ከተሰያዩ ጋዜጦች አነበብሁ፡፡ እነዚህ ትናንት ቅንጅት የነበሩ ነገር ግን ከውስጥም ከውጭም በገጠሟቸው ችግሮች በነበሩበት እንደነበሩ መቀጠል ያልቻሉ፣በሁኔታዎች ተገደው፣ ስምና አርማቸውን ተነጥቀው፣ አብረዋቸው የነበሩ ጥቂት የትግል ጓደኞቻቸው ተለይተዋቸው በአዲስ ስም በአዲስ ወኔ ብቅ ያሉ ሊደገፉ ሊበረታቱ የሚገባቸው ናቸው፡፡

ያሳለፍነው ሶስት ዓመት በፖለቲካው መድረክ የእርስ በርስ ግጭቶች የተካሄደበት፣ ክህደት እንደ ጀብድ ደረት ያስነፋበትና በአሉባልታ ስራ የነበረበትና ስም ማጥፋት እፍረት ያልሆነበት በተጓዳኝ ደግሞ ሞት፣ እስራት፣ ስደት ከቤት መፈናቀል የአካል መጉደል የተስተናገደበት ወቅት ነበር፡፡

ይህን ሁሉ አልፎ በዕናት መገኘትና ተገቢውን ተግባር አከናውኖ እንደገና ወደ ሀዲድ መግባት መቻል በራሱ ታላቅ ተግባር ቢሆንም ጉዞው ከመጀመሩ በፊት ከትናንት መማርን በተጨባጭ የሚያሳይ ተግባር በጥንቃቄ መከናወን አለበት፡፡ ለዚህ ተግባር ደግሞ ይጠራል የተባለው ጠቅላላ ጉባኤ ወሳኝ ነው፡፡

ድምፅ የሚያገለግለው ምርጫ ቦርድ ለሚያዘጋጀው ምርጫ ብቻ መሆን የለበትም፡፡ የፖርቲ አመራሮችንም ለመምረጥ ድምፅ በተገቢው መንገድ ስራ ላይ መዋል አለበት፡፡ ጠ/ጉባኤ ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንዱና ዋነኛው ምርጫ በመሆኑ የጠ/ጉባኤው ተሳታፊዎች ማንን እና ለምን መምረጥ እንዳለባቸው ወስነው ይህንኑ ውሳኔያቸውን ያለምንም ይሉኝታና ፍርሃት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የትናንቱ ቅንጅት አመራሮች ከተጣማሪ ፖርቲዎች በኩታ የተወጣጡ ቢሆንም በቅንጅቱ ጉባኤ ይሁንታ አግኝተው ተጨብጭበሳቸውና ተወድሰው ነበር፡፡ ግን ውጤቱ ምን ሆነ ራሳቸው መሪ የሆኑበት ወይንም የሆኑለት ፖርቲ ህጋዊ ዕውቅና እንዳያገኝ እጥብቀው የታገሉ፣ ከዚህ አልፈውም ልንከሰስ ስለሆነ ቅንጅትን እንተወውና በየጎጆአችን ገብተን እንመሸግ ያሉ፣ ይህ ሃሳብና ፍላጎታቸው ተቀባይነት ቢያጣ ጥቂት ተከታዮቻቸውን አስከትለው ተግባራዊ ያደረጉና ይህንንም እንደ ጀብድ ያወሩት በጉባኤ «የተመረጡ» ነበሩ፡፡ ያኔ እጅ አውጥተው የመረጧቸውና አጨብጭበው የተቀበሏቸው በኋላ በድርጅታቸው ቢያዝኑ ምን ረባ!

አብረው በጋራ የወሰኑትን ውሳኔ ሰመሻር ጊዜ ያልፈጀባቸው እንደውም ውሳኔውን አጣጥለው ሂደቱን ህገ-ወጥ ብለው የትግል ጓደኞቻቸው ላይ ከመመስከር ያልተናነሰ ተግባር የፈፀሙ ሰዎች እንደዚሁ ዘጉባኤ የተመረጡ ተብለው የተደስኮረላቸው ነበሩ፡፡

ያለምንም ተቃውሞ በስምምነት እንደተወሰነ የተነገረለት የቅንጅቱ ም/ቤት ውሳኔ የሁሉንም የም/ቤት አባላት ይሁንታ አግኝቷል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ሌላው የፖርቲው አባል ቢቀር ቢያንስ ውሳኔውን አብረው የወሰኑት የም/ቤት አባላት ለተፈፃሚነት ሊሰሩና ሊያከብሩት ግዴ ይላቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ሁኔታዎች መልካቸውን ሲቀይሩ ወኔ የከጻቸው ውሳኔውን እየጣሱ እጅ መስጠታቸው አይዘነጋም፡፡ ከዚህ የባሰው ግን አብረው የወሰኑትን ውሳኔ የጥቂቶች ብቻ ውሳኔ ነበር በማለት ጥቂት እንኳን ሃፍረት ያልተሰማቸው መሆኑ ነው፡፡ ይህን የፈፀሙትም «ተመርጠው» የላዕላይ ም/ቤት አባል ለመሆን የበቁት ናቸው፡፡

ችግሮች በውይይት የሚፈቱበትን መንገድ በመፈለግ ልዩነትን በማጥበብና መቻቻልን በመፍጠር አንድነትን ከማጠናከር ይልቅ አሉባልታ እየፈጠረ፣ ትናንህ ልዩነቶችን እያገዘፈና የመቻቻልን በር እየዘጉ የፖርቲውን ህልውና ለማጥፋት ጉልህ ባለድርሻ የሆኑት ተግባር የፈፀሙት ሰዎች በጉባኤ ተመርጠዋል ተብለው ለኃላፊነት የበቁ ናቸው፡፡

በተቀመጡበት ኃላፊነት የሚመጥን አመራር በመስጠት መልካም የመልሶ መቋቋሚያና የሽግግር ጊዜ ከመፍጠር ይልቅ ጎራ ለይቶ መለሰፍን የእኔ የሚሉትን ወገን መርጦ መጽለትን ስራ ያደረጉት ከዚህ በከፋም ህገ ደንብ እየጣሱ እርስ በእርስ እየተሿሿሙ ፖርቲው ዛሬ በደረሰበት እንዲበቃ ያደረጉት የፖርቲ መሪ ተብለው በጉባኤ የተመረጡና የተጨበጨበላቸው ነበሩ፡፡ አሁን እንድነት በሚጠራው ጉባኤ የሚሳተፋት ከምላ ጎደል እንደውም ሙሉ በሙሉ ከላይ በጠቀስነው ሂደት ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ ትናንት የመረጣችኋቸው የስሩትን አጢኗችሁ ከዛ ተምራችሁና ተቀጥታችሁ ነው ወይ ወደ ጉባኤ የምትገቡት? ነው ጥያቄያችን፡፡ ያለፈን እንዳይደገም የሚያስችል ተግባር ለማከናወን ብርታቱም ጥንቁቅነቱም ይኑራችሁ ነው መልዕክታችን፡፡

የአንድነት ጉባኤ ተሳታፊዎች ለሁላችንም የመታገያ መድረክ ሊሆን የሚችል ፖርቲ ለመፍጠር ከልብ ወስናችሁና ትናንት ከደረሰው ሁሉ ተምራችሁ ከሆነ የስልጣን ጥም የሚያናውዛችሁ ሳይሆን የሐገር ጉዳይ እንቅልፍ የሚነሳችሁ ለመምረጥ ድፍረቱም ብልሃቱም ሊኖራችሁ ይገባል፡፡

ልታይ ልታይ ባዩች ዝናና ጥቅም ናፋቂዎች የማስመሰል ክህሰ-ታቸው ሬቂቅ በመሆኑ እታለዋቸሁ ወይንም አምታተዋቸሁ ሊሰሩበት ሳይሆን ሊታዩበትና ድብቅ ዓላማቸውን ሊያራምዱበት ወደሚያልሙት ቦታ እንዳይወጡ በጥንቃቄ መስራት ይኖርባችኋል፡፡ አፈ ጮሌዎች የሰሩትን አይተናል፡፡ ለዚህ ህዝብ እንሞታለን እያሉ ሲፎክሩ የነበሩ እንካ;ን ሞትን አስራትን መጋፈጥ ሲሳናቸው ተመልክተናል፡፡ ወገበር ለማሞት አይደለም የተመረጥነው ብለው እኛ ን (ህዝቡን) አሳስተው እነርሱ ግን ከወንበሩ ላይ በመታየት ጊዜ እንዳልወስደላቸው አይተናል፡፡ እናም በምላስ አታሉ በፋከራ ታጋይ(ማንዴላን) መስሉ ቦታ ማግኘት ዛሬ ጊዜው አልፎበታል በማለት ይህን በተግባር ማሳየት መቻል አለባችሁ፡፡ በግልፅ በመፎካከር እንጅ በድርጅታዊ ትብትቦ በማሰር ማንንም ማታለል እንደማይቻልና በዚህም መንገድ የፈለጉትን ማግኘት እንደማይሳካ በድምፃችሁ ማረጋገጥ አለባችሁ፡፡

ለስም ሳይሆን ለተግባር ቅድሚያ ስጡ፡፡ ከስም የሚቀድም የክብርም የማዕረግም ስም ይዘው ስንት እንቱ የተባሉ ሰዎች በተግባር ኮስሰው በእምነት እንሰው ተመልክተናል፡፡ በሃብት ሳይሆን በዕናት መገኘት መቻል ላይ ትኩሩ፡፡ ነገም ሌላ ቀን ነውና ትግሉ እየጠነከረ ሲሄድ የሚሆነው አይታወቅምና፣ ለታላቋ ውሃ የሚታመኑ በእምነታቸው የሚፀኑ የስልጣን ፍላጎት ሳይሆን የትግል ጥማት ያላቸውንና ይህንንም ባለፈው የችግር ጊዜ በተግባር ያሳዩ ሰዎችን ለመምረጥ ብታቱ ይኑራችሁ፡፡

የበግ ለምድ የለበሱ የቀበር ባህታዊያን ከመካከላችሁ በመግባት ከመነሻው ለቆጣጠሯችሁ አልያም ጤና ሲነሳችሁ ማቀጻቸው ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ይህንን ያለመጠርጠር ከትናንት ያለመማር ብቻ ሳይሆን ያለ-በትንም ወቅትና ሁኔታ ያለማወቅ ትልቅ ድክመት ነው፡፡ ስለሆነም በዕጩነት ስለሚቀርቡ ሰዎች በጉባኤው አዳራሽም ሆነ በቡናና ሻይ ሰዓት በደንብ ተወያዩ፡፡ መረጃ ተለዋወጡ፡፡ ወደ ሃሳፊነት ከወጡ ለፖርቲው አደጋ ሊሆኑ

ነገም ሌላ ቀን ነውና ትግሉ እየጠነከረ ሲሄድ የሚሆነው አይታወቅምና፣ለታላቋ ውሃ የሚታመኑ በእምነታቸው የሚፀኑ የስልጣን ፍላጎት ሳይሆን የትግል ጥማት ያላቸውንና ይህንንም ባለፈው የችግር ጊዜ በተግባር ያሳዩ ሰዎችን ለመምረጥ ብታቱ ይኑራችሁ፡፡

ከንጋቱ ዘገየ

የሚችሉ ሰዎች እጩ ሆነው ካጋጠሟችሁ ስለ እነርሱ የምታውቁትን ለማያውቁት የጉባኤ አባላት ሹካፍሉ፡፡ ዛሬ በግዴለሽነት ከታሰፈ ነገ ሊሆን የሚችለውን አስቡ፡፡ እየገነቡ ማፍረስ እየሰበሰቡ መበተን ዛሬ በእኛ ይብቃ በሉ፡፡

የአንድነት ፖርቲ ጠቅላላ ጉባኤ ተሳታፊዎች ዋነኛ ትኩረታችሁ ምርጫው መሆን አለበት፡፡ ደንብና ኘሮግራም በየደረጃው ብዙ ተብሎ-በትና ተሰርቶበት የሚቀርብ በመሆኑ በአሰራርም ጠ/ጉባኤ ለነዶችን መርምሮ ማዕደት እንጅ በጥልቀት ቃል በቃል መወያየት የሚያስፈልገው በመሆኑ ጊዜ የሚወስድባችሁና ብዙ የሚያወያያችሁ ሊሆን አይችልም፡፡ አይገባም፡፡ ከፖርቲው ዓላማ የተቃረነ ለአሰራርም አስቸጋሪ የሆነ ጉዳይ አለ ከተባለ በዚሁ ላይ ብቻ መነጋገር በቂ ነው፡፡

ጉባኤያችሁ እንደ መስራት የሚቆጠር በመሆኑ ሪፖርቱን መነሻ በማድረግ ስለ ትናንት ሰመወያየት እትችሉም፡፡ አስፈላጊም አይደለም፡፡ ምክንያቱም መስራት ያለባችሁ እንጂ ራሳችሁ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን እንደ ምርጫ ቦርድ ፍላጎትና እንደ ህጉም አግባብ ነውና፡፡

ስለሆነም ሙሉ-ትኩረታችሁን ስጥታችሁ መስራት ያለባችሁ ስለምትመርጧቸው ሰዎች መሆን አለበት፡፡ ከህደት እንጂ ጀብድ እየተቆጠረ ማሳፈሩ ቀርቶ ደረት ማስነፋት ጀምሮአል፡፡ ነገ የፈለጉትን ሳያገኙ አልያም ወኔ ሲከዳቸው ትግሉን ለመክዳትና የትግል አጋሮቻቸውን አሳልፈው ከመስጠት ያ የማይመሰሉ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ሳይሆን ለስልጣን የሚታገሉ ሰዎች ወደ ሚያታዣቸው የስልጣን ቦታ እንዳይደርሱ በድምፃችሁ ልትገድቧቸው ይገባል፡፡ ይህን ማድረግ ከቻላችሁ በእርግጥ ከትናንት ተምራችኋል ማለት ነው፡፡

የሰይጣኖች መፈንጫ . . .

ተሸጋጋሩ፡፡ ይኸውም በውጊያው የተመናመነውን የተከታተቻቸውን ቁጥር ለማሳደግ ከ18 አመት በታች የሆኑ አምቦቶችላ ልጆችን መሳሪያ በማስታጠቅ ኤል.አር.ኤን ማጠናከር ነበር፡፡ እነዚህን ልጆ-ተፋላሚዎች የሚያገኙ-አቸው በሚገኙሳተራቢት ለሚን ኦ-ጋጋላ አካባቢዎች የሚገኙ ልጆችን በማፈን ከዚያም የልጅ እአምሮአቸውን በመመረዝ ማንኛውም ሰውትድርና ዕድሜው የደረሰ ሰው ወታደር ከመሸኑ በፊት መትስም የሚጠበቅበትን ወታደራዊ ስልጠና ከሚችሉትና ከሚቋቋሙት በላይ ከተሰጣቸው በኃላ ነበር፡፡ እነዚህ ህፃናት ከቤተሰቦቻቸው እቅፍ፣ ከመንገድ፣ ከትምህርት ቤት እየተሰቀሙ እንዴት መገደል እንዳለባቸው ትምህርት ተስመው ገድያውንም ከቤተሰቦቻቸው እንዲጀምሩ ተደርገው ሞትንም ሆነ መሞትን ከትንጣት የማይቆጥሩ የለየላቸው የሰው ልጅ አውራዎች ከተደረጉ በኋላ ብቁ ወታደሮች መሆናቸው ተነግሮአቸው ወደ ተልእኮአቸው ይሰማራሉ-ወደ ሞትና ጥፋት ተልእኮ ፡፡

ኤል.አር.ኤ እነዚህን «ሕውሬ የልጅ-ወታደሮች በመጠተም መጠኑ-ሰፊ ጥቃቶችን በሙሲቪኒ ወታደሮች ላይ በማድረስ ሙሲቪኒ የሚመሩትን ህዝብ ደህንነት ለመጠበቅ እንደተሳናቸው ማሳየት በመቻሉ እንዲሁም በሙሲቪኒ ሰራዊት ውስጥ የተወሰኑ አባላት በሚወስዱት የጭካኔ እርምጃዎች በእጅጉ የተቀየሙ የእዝሊሊ ተወላጆችንና በሰሜን ኡ-ጋንዳ የሚኖሩ ነዋሪዎችን ልብ ለመግዛት በመቻሉ የተወሰነ የህዝብ ድጋፍ ለማትረፍ ችሉ የእደገን ሳቱክ የሽምት ውጊያ ስትራተጂ መጠነኛ ውጤት አመጣ፡፡

ይህ የተወሰነ ህዝባዊ ድጋፍ በ1991 ተመናመነ፡፡ በተጠተሰው አመት የሙሲቪኒ መንግስት ባካካሄደው ወታደራዊ ዘመቻ ኤ.ል.አር.ኤን ለማስወገድና ዋነኛ የድጋፍ ምንጭ የሆኑትን ህዝቦች ለመመለስ በድምፅ አሰባ መሳሪያዎች ብቻ /ከጦር እና ተስ-ት/ የታገዘ ጥቃት በቡድኑ ላይ አካሄደ፡፡ በዚህ «ዘመቻ ሰሜን» ተብሎ በተሰየመው ዘመቻ ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎችን የታጠቀውን ኤል.አር.ኤን አልበገረውም፡፡ ያም ቢሆን ዘመቻውን ለመፈፀም የህዝቡን ድጋፍ በማግኘት ህዝቡን በዘመቻው ተባተፉ እንዲሆኑ ሙሲቪኒ ተሳክቶላቸው የነበረ በመሆኑ ስኬቱም ኮኒን ያስባፈጨ ከዚህም በኋላ የህዝቡን ድጋፍ መልሰው እንደማያገኙ በማመን ከሙሲቪኒ ጋር ተባባሪ ነበሩ ያሏቸውንና በጠቅላላ ጨፈጨፏቸው፡፡ ሙሲቪኒ ያደረጉት ዘመቻ ቢከሽፍም ኤል.አር.ኤ በወሰደው እርምጃ አብዛኛው የሰሜን ኡጋንዳ ነዋሪ ከኮኒ በተቃራኒው አንዲሰለፍ አስገደደ፡፡

በጆሴፍ ኮኒ ኤ.ል.አር.ኤ በአሁኑ ወቅት ወታደራዊ አመራርነቱን የሚመሩት ወታደራዊ አዛዦች ከ10 ወይም 12 አመት በፊት ታፍነው የተወሰዱ፣ከሞትና ጥፋት ሌላ ምንም የማያውቁ፣አፍንጫ፣ጆሮ፣ አንር ...

ወደ ገጽ 13 ዞሯል

www.abbaymedia.com